**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)**

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ሚያዚያ 23 ቀን 2001 ዓ.ም
May 1 2009

# የትግል ቀን በትግል ለማክበር

በመላው ዓለም ሜይ 1 የላብ አደሮች ቀንን ምንነትና ይዘት በማገናዘብ በብሄራዊ (በየሀገራቱ) ደረጃ እንዲከበር በተወሰነው መሰረት የላብ አደር ድርጅቶች፥ ለላብ አደሩ ቀና አመለካከት ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች፥ መንግሥታዊ ያልሆኑ የሲቪል ማኅበራት በጋራ ሆነው ቀኑን (እንደየሀገሩ ሁኔታ) በሰላማዊ ሰልፍ፥ የተለያዩ ላብ አደር ነክ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን በማዘጋጀት... በደመቀ አኳኋን ያከብሩታል። ላብ አደሩ ከሚደርስበት በደል በተጨማሪ በአለም አቀፍ ደረጃ በተከሰተው የኤኮኖሚና የፋይናንስ ቀውስ ክፉኛ እየተጠቃ፤ ለሥራ አጥነት እየተዳረገ፤ የሕክምና እንክብካቤው ዋስትና እያጣ፤ ለጡረታ ጊዜው የሚያገለግለው ላቡን አንጠፍጥፎ የከፈለው ገንዘብ ዋጋውም ሆነ የመከፈሉ ሁኔታ አሰተማማኝነት እየመነመነ፤ በበርካታ ታዳጊ ሀገሮች የሚገኘው ላብ አደር ደግሞ የሚደርስበት የመብት ረገጣ፤ የነጻነት እጦት፤ ዴሞክራሲያዊ አየር አለመተንፈስ፤ ራሱንም ሆነ ቤተሰቡን ከኑሮ ውድነት ለመቋቋም የሚያስችለው በቂ ደሞዝ አለማግኘትና ሌሎችም ችግሮች ይበልጥ ከድጡ ወደ ማጡ በመሆን እያሰቃዩት በመሆናቸው የዘንድሮውን የላብ አደር ቀን አከባበር ልዩ እንደሚያደርገው እሙን ነው።

በ1889 ዓ.ም. ዓለም አቀፍ የሠራተኞች ማህበር ሲቋቋም - ሜይ 1 የትግል ቀን ሆኖ እንዲከበር ሲወስኑ - ማጠየቂያዎቻቸው በ19ኛው መቶ ክ/ዘመን የላብ አደሩ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ሁኔታ በጣም አሰቃቂና አሳዛኝ በመሆኑ ሲሆን፥ ይህንን ለመቋቋምም የራሱን የላብ አደሩን ድርጅት መስርተው ለመታገል በሚልም ነበር። በወቅቱ ሜይ 1 የትግል ቀን ተብሎ ሲወሰን የሥራ ሰዓት በቀን 8 ሰዓት እንዲሆንና ሌሎቹም የላብ አደሩ ጥያቄዎች መልስ እንዲያገኙ ትግሉን ለመቀጠል ነበር። ዘንድሮም እንደእስከዛሬው የላብ አደሩ በርካታ ጥያቄዎች ያልተሟሉ ብቻ ሳይሆኑ በተለያዩ ምክንያቶች መብቶቹ በአሰሪዎቹና ለአሰሪዎቹ ጥብቅና በቆሙ መንግሥታት እየተገደቡበት ይገኛሉ። እጅግ ብዙ የሆኑ ጥያቄዎቹ ዛሬም ወቅታዊነታቸው እንዳለ ነው።

ከዚህ አንጻር ያለውን የሀገራችንን ሁኔታ ስንዳስስ፣ ላለፉት በርካታ ዓመታት የኢትዮጵያ ላብ አደሮች ኢሰአማን ለማቋቋምና ለማጠናከር፤ በየካቲት አብዮት እንቅስቃሴም ወቅት ጠቅላላ የሥራ ማቆም አድማ በማድረግ የተጫወቱት አቢይ ሚናን መጥቀሱ ተገቢ ነው። ይህንን ቀን ለማክበር ሰላማዊ ስልፍ ባደረጉ ኢትዮጵያዊያን ላይ የደረሰባቸው አሰቃቂ የግፍ ጭፍጨፋ፤ ለእስር ሆነ ለስደት መዳረጋቸውን ስናስታውስ፣ የላብ አደሩ ፖለቲካዊ፥ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ መብቶቹ እንዲከበሩና እንዲጠበቁ በነጻ ማህበሩ (ኢሰአማ) አማካይነት ጠንክሮ በመንቀሳቀሱና በመታገሉ፣ ይህ ሁሉ በደል ትግሉን ከቶም ሊገታ አለመቻሉን ነው የምንገነዘበው። ላብ አደሩ ከኢህአፓ ጎን በመሰለፍ ለመብቱና ለሀገሩ ያደረገው መራራ ትግል በሀገራችን ታሪክ ክቡር ቦታን ይዞ

ይገኛል። የላባደሩ መሪዎች አነማርቆስ ሃጎስና ሌሎችም መስዋዕት ሲሆኑ፤ ከሺህ ያላነሱ ወጣቶችና ሌሎች የኅብረተሰቡ ክፍሎች በአንድ ቀን (ሚያዝያ 23/1969) ሲጨፈጨፉ፣ አሁንም የላባደሩን ትግል ሊገታው አልቻለም ነበር።

ይህንን የዘንድሮውን ቀን ስናከብርና ስንዘክር ላለፉት አሥራ ስምንት አመታት የተጻፈበትን ወረቀት ያህል እንኳ ክብደት የሌለውን፤ ያውም የላብ አደሩ ፍላጎት ያልተጠየቀበትን የሰራተኛ ሕግ የመለስ አገዛዝ አውጥቶ በላዩ ላይ ጭኖበት ይገኛል። በተግባር የምናየውም፤ ላብ አደሩን በብሄረሰብ ደረጃ ከፋፍሎ መደባዊ አንድነቱን እንዳያረጋግጥ ከፍተኛ ጋሬጣ ሆኖበት፤ ማህበሩ በተለጣፊዎች ተነጥቆበት፤ ከአዲሶቹ ጸረ ሕዝብ ገዢዎች ብዝበዛ የሚከላከልበት ሕግና መብቱን ተነፍጎ፤ ሰብዓዊ መብቱ ተረግጦ፤ በሀገሩ በፈለገበት አካባቢ ሰርቶ የማደር ብቻ ሳይሆን ሥራውንም የማግኘት እድሉ እንኳ በዘርና በክልል ታጥሮበት ነው ያለው። ጸረ ኢትዮጵያ በሆኑ ክፍሎች አላግባብ ከሥራ መባረርና ከቀዬው በግዴታ መፈናቀል የእለት ጉርሱ ሆኗል። ሴት ላብ አደሮች አሁንም ከጾታ ባሻገር መደባዊ ጥቅማቸው ላይ አድልዎ ይደረግባቸዋል። ምንም አይነት የሥራም ሆነ የኑሮ ዋስታና ሳይሰጥ በብጣሽ ወረቀት ከሥራ መባረርና የጡረታ መብት መነፈግ የተለመደ ነው። እነዚህ ሁሉ በሀገራችን ያለውን የላብ አደሩን ሁኔታ ከሞላ ጎደል ባጭሩ የሚገልጹ ሲሆኑ፣ ላብ አደሩ እንዲወገዱ የታገለላቸው ችግሮች ከሌሎች ማህበራዊ ችግሮች ጋር ተደማምረው በከፍተኛ ደረጃ እያመሰቃቀሉት ይገኛሉ።

ዘንድሮም ይህንን ቀን ስናስታውስና ስናከበር ከነአበራ ገሙ፤ ዳሮ ነጋሽ፤ እስከነማርቆስ ሀጎስ ድረስ የተደረገውን የትግልና የመስዋዕት ክፍያ፣ በቅርቡ በድሬዳዋ የምድር ባቡር ላብ አደሮች እንደታየው አብቦ፤ ቀጣይነቱንና የትግል አሻራውን በአዲስ መልክ ለማሳረፍ፤ የግንባር ቀደም ሚናውን በትግል ለማስመስከር እየተንቀሳቀሰ መሆኑን በመገንዘብ ነው። ኢሕአፓ ለላብ አደሩ ያለውን ወገንተኛነት በመግለጽ የጀመረውን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በወያኔ አገዛዝ መቃብር ላይ ስኬታማ እንዲሆን በተቻለው ሁሉ በመጣርና የትግል አንድነቱንና ቃል ኪዳኑንም በማደስ ጭምር ነው። ላብ አደሩ በነጻ ማህበሩ የመደራጀት መብቱ ተነፍጎት፥ ለጭፍን ብዝበዛ ተዳርጎ፥ በኑሮ ውድነትና በአገዛዙ ጭካኔ እየተሰቃየ ባለበት ኢሕአፓ ከላብ አደሩ ጎን በመሆን የማህበሩ ሕልውና እንዲጠበቅ፤ የመለስ አገዛዝ አፋኝ እርምጃና ከፋፋይ ሴራ እንዲገታ፤ የኤኮኖሚ መብቱ እንዲከበር፣ አላማዎቹና ራዕዮቹ ከግብ እንዲደርሱ ለሚያረገው ትግል አጋርነቱን እየገለጸ ለችግሮቹ መፍቻ ዘዴዎችንም አብሮ ያፈላልጋል። ለላብ አደሩ መብት መከበር አሁንም እንደበፊቱ በሕቡዕ ሆነ በይፋ ለሚታገሉ መሪዎቹ አክብሮቱንና አድናቆቱን እየገለጸ አስከድል ድረስ በቁርጠኝነት ከጎናቸው በመቆም እንደሚታገል ያረጋግጣል።

በላብ አደሩ ቀንና ለላብ አደሩ ሲታገሉ የወደቁ ጓዶችና ላብ አደሮችን ሁሉ በአክብሮት እንዘክራለን!
የትግል ቀንን በትግል እናክብር!
ላብ አደሩ ምንጊዜም አቸናፊ ነው።



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France